# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

<u>በቤተ ክርቲያን የተዘጋጀ ታላቅ ሪትሪት</u>

ቀን፡ **7/4 - 7/6/2019**
**አድራሻ፡** W2511 WI-23, Green Lake, WI 54941 (Takes about 3 hours to 3:30 hours)
**Phone** = (920) 294-3323 Booking ID number= 14589
For making reservation please call during the below hours
**Sunday - Thursday 8:30-4:30**
**Friday - Saturday 24 hours**
**When reserving rooms please provide the date, the name Yemsrach how many people will be in the room.**

**<u>የጾምና የጸሎት አዋጅ</u>**

በፊታችን ባለው ሳምንት <u>እሮብ፣ ሐሙስና አርብ</u> ስለ ምድራችንና ስላለንበት ከተማ በመጾምና በጸሎት የእግዚአብሔርን ፊት እንድንፈልግ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። ሁላችንም እሮብና ኀሙስ በ7፡00 ፒ.ኤም. በ **<u>415-634-6763 access 661237#</u>** እንገናኝ። አርብ ደግሞ በአካል ተገናኝተን እንጸልያለን። ጌታ ይባርካችሁ።

**<u>የአርብ ፕሮግራም</u>**

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በተለይም ደግሞ አሁን ዶ/ር ተረፈ ስለ ምጽአት (eschatology) እያስተማረ ይገኛል። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
**773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)**
**773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)**
**630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)**
**773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)**
**773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)**

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?"
(ሮሜ 8:31)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.

**March 17, 2019** | **መጋቢት 8፣ 2011 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ................. | ወ/ም ፍቅሩ ቴንሶ |
| አምልኮ....................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወ/ም ረድኤቱ ግርማ ካሳ |
| ቃል ............. | ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

"እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን... ሰዎች በእኛ ላይ
በተነሡ ጊዜ፥
ቍጣቸውን በላያችን በነደደ ጊዜ፥ በዚያን ጊዜ
ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር፤
በዚያን ጊዜ ውኃ ባሰጠመን ነበር፥ በነፍሳችንም ላይ
ፈሳሽ ባለፈ ነበር፤
በዚያን ጊዜ የጐርፍ ውኃ በነፍሳችን ላይ ባለፈ ነበር።
ለጥርሳቸው ንክሻ ያላደረገን እግዚአብሔር ይባረክ።
ነፍሳችን እንደ ወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች፤
ወጥመድ ተሰበረ እኛም አመለጥን።"(መዝ. 124)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| **መሪ** | **ቀን** | **አድራሻ** |
| ወ/ም አያሌው አሰፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ኢያሱ -- እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሆነ አገልጋይ

*"በሕይወትህ ዕድሜ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም፤ <u>ከሙሴ ጋር እንደ ሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ</u>፤ አልጥልህም፥ አልተውህም...<u>በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና</u> ጽና፥ አይዞህ አትፍራ፥ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን?" (ኢያሱ 1፡ 5,9)*

ኢያሱ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን የሚፈልግ አገልጋይ ነበር። ሁልጊዜ የእግዚአብሔር ክብርና መገኘት ካለበት ከመገናኛው ድንኳን አይለይም። እርሱ እግዚአብሔርን ይፈልግ የነበረው ለጉዳዩ ብቻ ሳይሆን ለሕይወት ነበር። አስቀድም እግዚአብሔርን ይፈልጋል። ከዚህም የተነሳ በሚሰራው ስራ ሁሉ የተከናወነ አገልጋይ ነው።

እንዲሁም ደግሞ እያሱ እግዚአብሔርን በፈለገው መጠን እግዚአብሔር የተገኘለት አገልጋይ ነው። ግዚአብሔር ለሚፈልጉት ይገኛል። በጸሎት ወደ እርሱ ስንቀርብ ይሰማናል። ለዚህም ነው በኤርሚያስ 33:3 ላይ ቃሉ "ወደ እኔ ጩኽ፥ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ" የሚለን። እግዚአብሔርን ፈልጎ ያፈረ የለም። እግዚአብሔርን የሚፈልግ ይጸናል። (መዝ. 105:4) እግዚአብሔርን የሚፈልግ በሕይወት ይኖራል። (አሞጽ 5:6) እግዚአብሔርን የሚፈልግ ምህረትን ይቀበላል። (ሰፎ. 2:3) እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ደስ ይለዋል። (መዝ. 16:10) እግዚአብሔርን የሚፈልግ ለኑሮ የሚያስፈልገው ሁሉ ይጨመርለታል። (ማቴ. 6:33)

ኢያሱ እግዚአብሔርን በፈለገው መጠን እርሱ ደግሞ "ከአንተ ጋር አለሁ" ብሎታል። ከሙሴ ሞት በኋላ ህዝቡን ወደ ርስታቸው የማግባት ታላቅ ኃላፊነት የተቀበለው ኢያሱ ከተሰጠው ጥሪና አገግልግሎት ጋር የእግዚአብሔር አብሮነት ተስፋ የተሰጠው አገልጋይ ነው። እግዚአብሔር እራሱ በቃሉ "ከሙሴ ጋር እንደ ሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ" አለው። በሚሄድበትም ሁሉ አምላኩ እግዚአብሔር ከርሱ ጋር እንደሚወጣ ቃልን ተቀበለ። ኢያሱ ለተሰጠው ታላላቅ የድል ተስፋዎችና የመጽናቱ ምክንያት እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑ ነው። በሕይወት ዘመንህ የሚቋቋምህ የለም የተባለው እግዚአብሔር ከርሱ ጋር ስለሆነ ነው። ጽና፣ እይዞህ፣ አትፍራ፣ አትደንግጥ የሚለውን ትእዛዝ የተቀበለው ከእግዚአብሔር አብሮነት ተስፋ ጋር ነው።

ለኢያሱ በእስራኤል ሕዝብ ፊት ሞገስ የሆነለት የእግዚአብሔር ከርሱ ጋር መሆን ነው። ኢያሱ ሕዝቡን በተናገረ ጊዜ ሕዝቡ አንድ ነገር ብቻ ነበር ያሉት፡ "ያዘዝኸንን ነገር ሁሉ እናደርጋለን ወደምትልከንም ስፍራ እንሄዳለን። በሁሉም ለሙሴ እንደ ታዘዝን እንዲሁ ለአንተ ደግሞ እንታዘዛለን፤ <u>ብቻ አምላክህ እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር እንደ ነበረ ከአንተ ጋር ይሁን</u>።" (ኢያ. 1:16)

ወገኖቼ:- እኛም በአዲስ ኪዳን የተቀበልነው ትልቁ ተስፋ አማኑኤል ነው። አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከኛ ጋር ማለት ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ጸጋን እና እውነትን ተሞልቶ በህዝቡ መካከል አድሯል። እንኪያስ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቋቋመናል? ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣላ ይደቅቃል። የመውጊያውን ብረት ለሚቃወም ለእርሱ ይብስበታል።